# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ.** 237210

ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች** - አቶ. አካለወልድ ይልማ - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች** - 1. ወ/ሮ ሰላማዊት ግርማ } ጠበቃ መላኩ ሞቲ ጋር ቀርበዋል

2. አቶ ክብረቅዱሳን ኃ/ማርያም - } ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በሰበታ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉ በሰበታ ከተማ ቀበሌ 01 ዉስጥ የሚገኝ አዋሳኙ በምስራቅ መንገድ፤ በምዕራብ፣ በሰሜን፣ እና በደቡብ ምሪት የሆነ ሦስት ክፍል መኖሪያ ቤት እና ሁለት ሱቅ እንዲሁም የግድግዳ ግንባታዉ ተጠናቆ ጣሪያዉ ለቆርቆሮ ልባስ የደረሰ ክፍል ያለዉ ቤት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ እያሉ ያፈሩት ቤት መሆኑን ጠቅሳ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ተብሎ እንዲወሰን በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበችዉን ዳኝነት ተከትሎ፣ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40(3) መሠረት በክርክሩ ተሳታፊ በመሆን ያቀረበዉን ክርክር መሠረት በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ይህ ቤት የግሌ እንጂ የተጠሪዎች የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አይደለም በሚል ላቀረበዉ ክርክር መሠረት ያደረገዉ ቤቱን ታህሳስ 15 ቀን 2012 ዓ.ም በሰበታ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ፊት ተደርጎ በተረጋገጠ ዉል ከአቶ መሠረት ቶሌራ የገዛሁት ነዉ የሚል ነዉ፡፡

የወረዳዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉ ቤት አመልካች ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም ተደርጎ ስልጣን ባለዉ አካል ፊት ቀርቦ በተረጋገጠ ዉል ገዝቶ የባለቤትነት ማረጋገጫ የወሰደበት መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረበችዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበች ሲሆን፣ የግራ ቀኝን ክርክር ሰምቶ የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በዚህም በውሳኔው ባለመስማማት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበችዉ ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ፣ የሰበር አቤቱታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበች ሲሆን፤ ሰበር ሰሚዉ ችሎት በበኩሉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የእኔ ነው በማለት ባቀረበው ክርክር ላይ 1ኛ ተጠሪ መልስ በመስጠት ሳትከራከር ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለው ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሰበታ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ ላይ መልስ እንድታቀርብ አድርጎ ግራ ቀኙን አከራክሮ ወሳኔ እንዲሰጥ በትዕዛዝ መዝገቡን መልሶታል፡፡

አመልካች ህዳር 13 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ እኔ ጣልቃ የገባሁት እንደማንኛውም ተከሳሽ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.40(3) መሰረት እንጂ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.41 ወይም 358 አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40(3) መሰረት በተከሳሽነት ወደ ክርክሩ ገብቼ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.234 መሰረት የመከላከያ መልስ ሰጥቻለሁ፡፡ አንድ ተከሳሽ በሰጠው መልስ ላይ ከሳሽ መልስ  እንዲሰጥ የሚደረግበት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ በሌለበት መዝገቡ ወደ ስር ፍርድ ቤት ተመልሶ 1ኛ ተጠሪ መልስ እንድትሰጥ የተባለበት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 40(3)፣ 343(1) የሚቃረን ነው፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት መልስ አልሰጠሁም ብላ አልተከራከረችም፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ጸንቶ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2015 ባቀረበችው መልስ መዝገቡ ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለሱ አግባብ መሆኑን ጠቅሳ ተከራክራለች፡፡ 2ኛ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2015 በሰጠው መልስ የእኛ ንብረት ባልሆነው ንብረት ላይ ለረጅም ጊዜ ክርክር ከማድረግ ውጪ ሊገኝ የሚችል ጥቅም በሌለበት ወደ ስር ፍርድ ቤት ይመለስ ተብሎ ወሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት የአመልካችን አቤቱታ ደግፎ

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከራክሯል፡፡ አመልካች የካቲት 07 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን ወደ ወረዳዉ ፍርድ ቤት ሲመልስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 40(3) መሠረት ባቀረበዉ ዳኝነት ላይ 1ኛ ተጠሪ መልስ ለመስጠት ዕድል ያልተሰጣት መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ ነዉ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰዉ አመልካች በክርክሩ ተሳታፊ በመሆን ላቀረበዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ አከራካሪዉ ቤት የባልና ሚስት (የተጠሪዎች) የጋራ ንብረት ሳይሆን የግሌ ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ አመልካች ወደ ክርክሩ የገባዉ ተከሳሽን ለመተካት ወይም ከተከሳሽ ጋር ኃላፊነትን ሊሸከም የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት ሳይሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የግሉ እንጂ የተጠሪዎች ወይም የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አለመሆኑን በሚያቀርበዉ ክርክር አረጋግጦ መብቱን ለማስከበር መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ወደ ክርክሩ የገባበት ሁኔታ በባህሪዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 41 ስር የሚወድቅ እንጂ በአንቀጽ 40 ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ቤቱ የግሌ ነዉ በሚል በዝርዝር ባቀረበዉ ምክንያት ላይ 1ኛ ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት በማድረግ ግራ ቀኝን አከራክሮ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ፣ የስር ፍርድ ቤት ይህን ሳያደርግ ማለፉ በእርግጥም የ1ኛ ተጠሪን የመሰማት መብት የሚገድብ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ አመልካች ባቀረበዉ ዳኝነት ላይ ምላሽ እንድትሰጥ ሳያደርግ የሰጠዉ ዉሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ይህንኑ በማረም የ1ኛ ተጠሪን መልስ ሰምቶ ግራ ቀኝን አከራክሮ እንዲወስን መዝገቡን ወደ ስር የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመመለስ የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር በተመለከተዉ መሠረት በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 404418 ላይ ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት ታህሳስ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**መ/ዐ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም